# ኢትዮጵያን እየገዙ የሱዳን ጠበቃ መሆን አይቻልም

## ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ. ም.
May 29, 2008

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ August 8, 2007 በቀጥታ ለጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ በግልባጭ ደግሞ ለፓርላማውና ለክልል መስተዳድራት ግልፅ ደብዳቤ መጻፉ ይታወሳል። ከዚያ አኳያ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ከፓርላማው ምላሽ ባይገኝም ኮሚቴውና የድንበሩ ኑዋሪዎች ባደረጉት ከፍተኛ ማጋለጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ መልስ ለመስጠት ተገደዋል።

በኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ እስከ ወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ ድረስ የነበሩት ሁሉም መንግሥታት መሪዎች የውጭ ወራሪን በመመከት የኢትዮጵያን የግዛት ክልል ሳያስደፍሩ አልፈዋል። የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በ17 ዓመት ውስጥ ዓይነተኛ ቋሚ ተግባሩ አድርጎ የወሰደው ግን የአገራችንን ድንበር መመከት ሳይሆን አሳልፎ የመስጠትና የጥፋት ዘመቻ ማካሄድ ነው።

በ1992 ዓ. ም. (እ.ኤ.አ) ኢትዮጵያ የባሕር በር አያስፈልጋትም ብለው ለዓለም ታዛቢዎች በድፍረትና በሚያሳፍር አንደበት የተናገሩት የወያኔ/ኢሕአዴግ ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ ለፓርላማው May 20, 2008 የድንበሩን አስመልክቶ ባደረጉት ንግግር ጉዊን የተባለ የእንግሊዝ ሻለቃ ብቻውን የኢትዮጵያን ግዛት ዘልቆ የከለለበትን መስመር መቀበላቸውን ከተናገሩ በኋላ በዚህ መሠረት 300,000 (ሦስት መቶ ሺህ) ካሬ ሄክታር ለም መሬት ለሱዳን መሰጠቱን በትዕቢትና በማን አለብኝነት በይፋ አሳውቀዋል።

ጠቅላይት ሚኒስትሩ ንግግራቸውን በመቀጠል "በ1980 ዓ. ም. የሱዳንና የኢትዮጵያን የድንበር ጉዳይ ያጠኑት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሊቃውንት ባወጡት መግለጫቸው የሻለቃ ጉዊንን መስመር መቀበል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው ብለዋል" ሲሉ አስደምጠውናል። ይሁንና በ1980 ዓ. ም. የጥናቱ ቡድን መሪ የነበሩት ዕውቁ ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደ ማርያም በማግስቱ ለጀርመንና ለአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያዎች የሰጡት ቃለ መጠይቅ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለጥናቱ ቡድን የተናገሩት ፍጹም ሐሰት መሆኑንና በተጨማሪም የአፄ ኃይለ ሥላሴም ሆነ የደርግ መንግሥት የጉዊንን መሥመር እንቀበል የሚል ስምምነት እንዳላደረጉ አረጋግጠዋል። ታሪካዊ ጥናቱን ካከናወኑት አባላት መካከል አንዱ ብቻ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ሌሎቹ በሕይወት ባሉበት ባሁኑ ወቅት የኮሚቴውን የጥናት ድምዳሜ ፍጹም ገለባብጦ ማቅረብ የሚያሳየው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን ገጸ በረከት ለማቅረብ ምን ያህል የታሪክ መረጃዎችን እንደሚቀለብሱና ለአገራችንም ያላቸው ራዕይ ምን ያህል የጥፋት ራዕይ መሆኑን ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ በፓርላማ ንግግራቸው የሱዳን አገር ጠበቃና አጋር ሆነው ጠላትን በመከላከል በየድንበሩ የወደቁትን ጀግኖች ወገኖቻችንን ሲያወግዙና ሲኮንኑ ደግሞ፤

"የእኔ፣ የኔ ነው የእናንተን እንካፈል የሚል የኢትዮጵያን ተስፋፊነት አቋም ተሸክሞ ነው ያደረው፤ ይህን ተቀብሎ ነው ያደረው የሱዳን መንግሥት፣ ይህን ተቀብሎ ማደሩ ደግሞ እንደ ጅልነት ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፤ አርቆ አሳቢነትን ያመለክታል፣ የጋራ ጥቅም ማየትን ያመለክታል" ብለዋል።

ይህ አነጋገር ከአንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ይቅርና ከተራ ምንደኛ የማይጠበቅ ሲሆን፤ አገራችንን ምን ዓይነት ሕልውናዋን ከሚፃረር አደገኛ ሰው እጅ እንደ ወደቀች ያመለክታል።

እውነት መናገር እንደ ፍጹም ወንጀል የሚቆጥሩት ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ ስለተፈናቀሉት ኢትዮጵያዊያን ሲያብራሩ ደግመው ደጋግመው "አንድም ኢትዮጵያዊ ከእርሻው የተፈናቀለ የለም፤ ወደፊትም የሚፈናቀል ኢትዮጵያዊ የለም" ብለዋል። ሀቁ ግን የሚከተለው ነው፤

- የሱዳን ጦር አፍሶ ከወሰዳቸው ሠላሳ አራት(34) ኢትዮጵያዊያን መካከል ስድስቱ(6) የት እንደደረሱ እስካሁን አይታወቅም፤
- ሃያ ስምንቱ (28) ከካርቱም በ50 ማይል ርቀት በምትገኝ ሥንጃ በተባለች ከተማ ውስጥ በሱዳን እሥር ቤት ይገኛሉ፤
- ከሃያ ስምንቱ መካከል ጥቂቶቹ ሁለት ጊዜ በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ ሲያስረዱ፤
  1. ከእርሻ ቦታቸው በሱዳን ጦር ታፍሰው መወሰዳቸውን፤
  2. ከእሥረኞቹ መካከል አንድ የ65 ዓመት ሽማግሌ፣ ሁለት ሴቶች እንደሚገኙ ጠቅሰው የጠቅላላው የእሥረኛ ዕድሜ ከ18 እስከ 65 ዓመት እንደሚሆን፤
  3. የቀይ መስቀል ተወካዮች በMay 22, 2008 ዓ. ም. እንደጎበኟቸው፤
  4. ከፍተኛ የምግብ አለመስማማትና ሕመም ጉዳት እንዳለና ከእሥረኞቹ 6ቱ በጠና እንደታመሙ፤
  5. ለሁለት ወር የለበሱት ልብስም ከአገራቸው በታፈሱበት ጊዜ የለበሱት አንድ ልብስ ብቻ እንደሆነና፤
  6. አብዛኛዎቹ የአንድ ዓመት እሥራት ወይም የአንድ ሚሊዮን የሱዳን ፓውንድ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ የሁለት ዓመት እሥራት ወይ የሁለት ሚሊዮን የሱዳን ፓውንድ ቅጣት እንደ ተበየነባቸው ተናግረዋል።

ከዚህ ሌላ በቅርቡ አቶ ሙሌ ታረቀኝ የተባሉ በሚኒስትር ደረጃ የወያኔ/ኢሕአዴግ ዲፕሎማት "ሀገር ፍቅር" ለተባለ በዋሽንግተን ዲሲ ለሚገኝ ሬዲዮ ጣቢያ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ከአገራቸው መሬት ተይዘው ወደ ሱዳን የተወሰዱ እሥረኞች መኖራቸውን አምነው ለማስፈታት ጥረት እየተደረገ ነው በማለት የራሳቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር ተቃርነው እውነቱን ተናግረዋል። ይሁንና ውርደትና ውሸትን እንደ ማዕረግ ዕድገት እየቆጠሩት ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ መሬቱን ከነሰዎቹ ለሱዳን ማስረከባቸውንና የወገኖቻችን ኢትዮጵያዊነት በእርሳቸው ዓይን እንደተሠረዘ፣ ከተፈለገም ባለንብረቱ ሱዳን ያስብላቸው ከሚል የክህደት ስሌት የመነጨ መሆኑን ያስገነዝባል።

# ውድ ወገኖች ሆይ!

የኢሕአዴግ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መኖር ከኢትዮጵያ አለመኖር ጋር በጥብቅ የተሳሠረ መሆኑን ይህ የሽፍጥ ንግግር የበለጠ እንዲጎላ አድርጎታል። የሚቀጥለው የጠቅላይ ሚኒስትሩ አካሔድም ግልፅ ነው፤ ውሃ ገብና ለም መሬታችንን በአስቸኳይ ለአዲሷ የነዳጅ ዘይት ባለፀጋ ሱዳን በግል ለመቸርቸር ሲባል በቅርቡ የድርድሩን ዘገባና ንግግራቸውን ያለድንጋጤና በፀጥታ ላዳመጠው ፓርላማ ያቀርባሉ። የፓርላማ አባላት ደግሞ ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኛዎቹ እንደ "ፓሮት" ወፍ የሚነገራቸውን የሚደግሙ በመሆናቸው የቀረበላቸውን ፈርመው እንደሚያሳልፉት መገመት አያዳግትም። ይህን በአገራችን ሕልውና ላይ የተሳለውን ሰይፍ ለመስበር በከፍተኛ ፍጥነትና አንድነት መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል።

በእርግጥ አገራችን በሆዳሞች በታጀበው የጥፋት መልዕክተኛ ወያኔ/ኢሕአዴግ እጅ ወድቃ በዚህ ደረጃ መገኘት፣ በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ሰቆቃና  ውሃ ገብ ለም መሬት ለሱዳን መሰጠቱ በኢትዮጵያዊያን ላይ የቀሰቀሰው  ቁጣ በየቀኑ እየገነፈለ ይገኛል። ይበልጥ ደግሞ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለባቸውን ልዩነት ወደጎን ትተው አገርን ከጥፋት ለማዳን በአንድ ጎዳናና አቅጣጫ መራመድ መጀመራቸው በጣም የሚያበረታታ ነው። ተቃውሞውና አሰላለፉ የበለጠ እንዲጎለብትም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የራሱን አነሳሽነት በመጨመር የእንቅስቃሴው ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ አብዛኛዎች የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ የሬዲዮና የድረ-ገጽ መገናኛዎች የተሳተፉበት ግብረ ኃይል አቋቁሞ፤ June 2nd 2008 በዋሽንግተን ዲሲ ታላቅ ሕዝባዊ ተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ አቅዷል።

በተጨማሪ የታቀዱትን ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍና ሕዝባዊ ስብሰባ በሚመለከት በቅርቡ መግለጫ የሚወጣ መሆኑን እንገልጻለን።

ስለዚህም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በዋሽንግተን ዲሲ፣ በተለያዩ የአሜሪካ፣ የካናዳ፣ የአውሮፓና በሌሎችም አሕጉር ከተማዎች በሚደረጉ እንቅስቃሴዎችና ሕዝባዊ ስብሰባዎች ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርግ ሀገራዊ ጥሪ እናቀርባለን።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት በቆራጥ ልጆቿ ይከበራል!
ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኑር!

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
e-mail:-  leethiopia@yahoo.com